ውሻ ከአንዳችሁ እቃ የጠጣ ጊዜ (እቃውን) ሰባት ጊዜ ይጠበው።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ውሻ ከአንዳችሁ እቃ የጠጣ ጊዜ (እቃውን) ሰባት ጊዜ
ይጠበው።"» ሙስሊም ባስተላለፉት ደግሞ "አንዱን በአፈር በመቀላቀል ይጠበው።" የሚል ተዘግቧል።
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ውሻ እቃ ውስጥ ምላሱን ያስገባ ጊዜ እቃው ሰባት ጊዜ እንዲታጠብ አዘዙ። ከነዚህ ሰባት ትጥበቶች የመጀመሪያውን በአፈር ቀላቅሎ ይጠበው ይህም ከዛ በኋላ ውሃ በተደጋጋሚ እንዲፈስበት ነው። በዚህም ከነጃሳውና ከጉዳቶቹ የተሟላ መፅዳት ይገኛል።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/3143